ኢ.ሕ.ባ.ማ
EBA

# ተሟጋች
# TEMUAGACH

በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የሚዘጋጅ

1ኛ ዓመት ቁጥር 12 ነሐሴ 2001

## ርዕሰ አንቀፅ

### የፍትህ ሥርዓቱና የሕግ ሙያ ማህበራት

በአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እንዲሁም ማህበራዊ ሁነት ውስጥ ሕግ እና ሕጋዊነት ላቅ ያለ ሚና አላቸው። ሕጋዊነት የተረጋጋና ሠላማዊ ማህበረሰብን ከመፍጠር ባሻገር በአንድ ሀገር የፖለቲካ መዋቅር ውስጥ መተማመንን እና በመጪ ሁኔታዎች ላይ እርግጠኝነትን በማስፈን ረገድ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው።

ይኽንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ መርህ ከማስፈን አኳያም መንግስት የራሱ የሆነ ትልቅ ድርሻ ቢኖረውም ሃላፊነቱን ሙሉ ለሙሉ በመንግሥት ላይ መጣል የተፈለገውን ውጤት አያመጣም። የሕግ ባለሙያዎችም የራሳቸው የሆነ ታላቅ ድርሻ አላቸው።

የሰው ልጅ በኑሮው ሂደት ውስጥ ትልቅ ቦታ ለሚሰጣቸው ሦስት መሠረታዊ መብቶች መከበር ማለትም የህይወቱን፣ የንብረቱን እንዲሁም የግል ነፃነቱን መጠበቅ በተመለከተ የእነዚህ ባለሙያዎች አስተዋፅዖ ታላቅ ነው።

ሞያተኞቹ ይህንን ተግባራቸውን በአግባቡ እንዲፈፅሙ ያስችላቸው ዘንድም በማህበር በመደራጀት ጥቅሞቻቸውንም ሆነ የሀገሪቱን ሕግጋት በተገቢው ሁኔታ የሚያስከብሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ህጋዊነትን በማስፈን ረገድ በእጅጉ ጠቀሜታ አለው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በማህበር የመደራጀት መብት በተፈለገው ሁኔታ ለሕጋዊነት መከበር ድርሻ የሚኖረው በነፃና ያለምንም ተፅዕኖ የተደረገ እንደሆነ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ ሙያተኞቹ ሕግንና ሕጋዊነትን ለማስከበር ያላቸውን ድርሻ መወጣት ቀርቶ እራሳቸው ሕጋዊነትን የሚጥሱበት፤ አልፎም የራሳቸውን መብት እንኳን የማያስከብሩባቸው አጋጣሚዎች ሰፊ ይሆናሉ።

በአሁኑ ወቅት ከሞላ ጎደል በሁሉም የአለም ሀገራት የሕግ ሙያ ማህበራት የተቋቋሙ ቢሆንም አወቃቀራቸውና ሕጋዊነትን በማስከበር ረገድ ያላቸው ድርሻ ይለያያል። አንዳንድ የአደጉ ሀገራትን ተሞክሮ በምንመለከትበት ጊዜ የሕግ ሙያተኞች ነፃ ሆነው በመደራጀት የፍትህ ሥርዓቱ አጋዥ በሆነ ሁኔታ ሲሰሩ ይታያል። እንደእነዚህ ባሉ ሀገራት የሕግ ሙያ ማህበራት ራሳቸውን የሚመለከቱ አንዳንድ ሁኔታዎችን በነፃነት ከመወሰናቸው ባሻገር ማህበራቱ የሚተዳደሩበት ልዩ ሕግ አላቸው።

በአንፃሩ በታዳጊ ሀገራት የሕግ ሙያ ማሕበራት ከተፅዕኖ ውጪ አይደሉም። የራሳቸው ሕግጋት ወጥቶላቸው ለመተዳደር ባለመቻላቸው እንደ አንድ ተራ ማህበር መቆጠር እጣ ፋንታቸው ሆኗል። ስለሆነም ስለ ሕግ እና ሕጋዊነት ተጨናቂ ነን የምንል ሁሉ ስለ ሕግ ሙያ ማህበራት ነፃነትና ስለሚያስተዳድሯቸው ሕግጋቶች ትኩረት ሰጥተን ልናስብበት ይገባል እንላለን።□

## በምስራቅ አፍሪካ በፍትህ ተደራሽነት ላይ የመጀመሪያው ስብሰባ ተካሄደ

የካናዳ ጠበቆች ማህበር ከዩጋንዳ አቻው ጋር በመተባበር ‹በምስራቅ አፍሪካ የፍትሕ ተደራሽነትን ማጠናከር› ከተሰኘ ፕሮግራም ጋር በተያያዘ እ.አ.አ ከመስከረም 2 እስከ 4 2009 ዓ.ም. በዩጋንዳ ካምፓላ የመጀመሪያውን አካባቢያዊ ስብሰባ አድርጓል።

በዚሁ ክልላዊ ስብሰባ ላይ ከኢትዮጵያ፣ ከዩጋንዳ፣ ከኬንያና፣ ከታንዛንያ ፍ/ቤቶች፣ ከፍትህ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ ከፍትህ ማሻሻያ ተቋማት፣ ከጠበቆች ማህበራት እንዲሁም ከካናዳ የተውጣጡ በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላቸው ባለስልጣናትና ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

ክልላዊ ስብሰባው ከተወያየባቸው አጀንዳዎች በዋናነት በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙና ከላይ በተጠቀሱት አራት ሀገራት የፍትህ ተደራሽነትን ማሻሻል ሲሆን የየሀገሮቹ የፍትህ ሥርዓት ውስጥ

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

### የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔውን በቅርቡ ያካሂዳል

ከተመሠረተ ከ43 ዓመት በላይ የሆነውና የዓለም ጠበቆች ማኅበር፣ የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት (ፓሉ) መሥራች አባል የሆነው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የሕግ ባለሙያዎች ማኅበራት በልዩ ሕግ እንዲቋቋሙ ተጠየቀ

የሕግ ባለሙያዎች ማኅበራት ማቋቋሚያ ልዩ ሕግ የሌላቸው የአፍሪካ አገሮች ብሔራዊ የሕግ ሙያ ማኅበራት በልዩ ሕግ እንዲመሠረቱና ሙያውን በመምራትና በመቆጣጠር ተገቢ ሚና እንዲኖራቸው በማድረግ የበኩላቸውን ገንቢ እርምጃ እንዲወስዱ የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት (ፓሉ) ጥሪ አደረገ።

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነበት የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት (ፓሉ) ይህን ጥሪ ያደረገው ባለፈው ሐምሌ ወር አጋማሽ ላይ የድርጅቱን የምክር ቤትና የኮንፈረንስ ስብሰባ አዲስ አበባ ውስጥ፣ በአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን አዳራሽ ከአደረገ በኋላ በስብሰባው ማጠቃለያ ባወጣው መግለጫ ነው።

ፓሉ በዚህ መግለጫው የሕግ ባለሙያዎችና የጠበቆች ማኅበራት በአፍሪካ ኅብረት አባል አገሮች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ ባሕላዊ፣ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ፣ እንዲሁም በሌሎች

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በባህር ላይ ውንብድና የተጠረጠሩትን በኬንያ መዳኘት መሠረታዊ መብታቸውን ይጥሳል ተባለ

በባህር ላይ ውንብድና የተጠረጠሩ ሶማሊያውያን በኬንያ መዳኘታቸው መሠረታዊ የሰብዓዊ መብታቸውን የሚነካ መሆኑን ጠበቆችና የመብት ተከራካሪዎች አስታወቁ።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ወቅታዊ ጉዳይ

# የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት አካሎች ስብሰባ፣ ሐምሌ 11 እና 12 ቀን 2001፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## የስብሰባዎች ማጠቃለያ የአቋም መግለጫ

የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት ምክር ቤት ስብሰባ 4ኛው ኮንፈረንስ ከመካሄዱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ተካሂዷል። ይህንንም ተከትሎ አራተኛው የኅብረቱ ኮንፈረንስ አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ዋና ጽ/ቤት አዳራሽ ተደርጓል።

በሁለቱም የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት አካላት ውይይት የተደረገላቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ነበሩ።

- የተሰናባቹ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርቶችና የሥራ ጊዜ ማጠቃለያ ተግባሮች፣
- የአፍሪካ አህጉር የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ፣ ሰላምና ደህንነት፣
- የአፍሪካ ኅብረት ዕድገት፣ ክፍለ-አህጉራዊ የኢኮኖሚ ማኅበረሰቦችና ክፍለ-አህጉራዊ ድርጅቶች፣
- በአፍሪካ ሕጋዊነት፣ የዳኝነት ነፃነትና የሕግ ሙያ ማኅበራት ያሉበት ሁኔታ፣
- በኒጀር በቅርቡ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት በመጣስ፣ የሥልጣን ክፍፍልን መርህ በመፃረር፣ የአገሪቱን ሕገ-መንግሥታዊ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻር፣ ሕገ-መንግሥታዊ ፍርድ ቤቱንና ፓርላማውን በመበተን፣ በሕግ ሳይሆን ራሳቸው በሚያወጡት ድንጋጌ (decree) በመመራት የሥልጣን ዘመናቸውን ለሦስተኛ ጊዜ ለማራዘም እያካሄዱ ያሉት ሕገ-ወጥ ተግባር፣
- የአፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት በምዕራብ አፍሪካ አገሮች የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ፍርድ ቤት ስለሚኖረው ሚና፣

በኅብረቱ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ሚ/ር ሮዲኒ ግሪጎሪ ሙር፣ የአሜሪካ ብሔራዊ ጠበቆች ማኅበር ፕሬዚዳንት፣ ሚ/ር ቤን ኪዩኬ፣ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን የሕግ አማካሪ፣ ሚ/ር ጂሴፔ ቢስኮንቲ፣ የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት የክብር ፕሬዚዳንትና መሥራች አባል፣ ዶ/ር ሞ ኢብራሂም፣ የሞ ፋውንዴሽን ፕሬዚዳንት ንግግር አድርገዋል።

የሞሮኮ አልጋ ወራሽ ልዑል አል ሀሰን ቢን ታላል የቪዲዮ መልዕክት ለስብሰባ ተሳታፊዎች አስተላልፈዋል። እንዲሁም የኅብረቱ የክብር የዕድሜ ዘመን ፕሬዚዳንት የሆኑት የሴኔጋሉ ፕሬዚዳንት አብዱላይ ዋዴ ለኮንፈረንሱ ያስተላለፉት መልዕክት በሴኔጋል የአፍሪካ ኅብረት ቋሚ መልዕክተኛ ተነቧል።

የአፍሪካ ልማት ባንክ የሕግ አማካሪ ሚ/ር ካሊዱ ጋዲዮ በአፍሪካ ኢንቨስትመንትና የንግድ ልውውጥ ሂደት ስላለው የሕግ ምክር አገልግሎት ፈንድ ገለፃ አድርገዋል። በዚህ በኩል የአፍሪካ አገራት ሥልጠናና አቅም ግንባታ እንደሚያስፈልጋቸው ጠቁመዋል።

የሞ ኢብራሂም ፋውንዴሽን ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሞ ኢብራሂም በበኩላቸው ለኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች ባደረጉት ንግግር ለአፍሪካ መልካም አስተዳደር መገንባትን፣ በዚህም ውስጥ የሙያና ቢቪክ ማኅበራትን የማጠናከር አስፈላጊነት፣ ጅምር ክፍለ-አህጉራዊ የኢኮኖሚ ማኅበረሰቦችን በማጠናከር የአፍሪካን የኢኮኖሚ ውህደት ማፋጠንን በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት ዶ/ር ሞ ኢብራሂም በአፍሪካ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንዲጠናከር በማድረግ ላይ ላሉት አስተዋፅኦ ዕውቅና በመስጠት ሸልሟቸዋል።

የአሜሪካ ብሔራዊ ጠበቆች ማኅበር ፕሬዚዳንት ሚ/ር ሮድኒ ግሪጎሪ ሙር በማኅበራቸውና በመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት መካከል ያለውን ትብብር የማጠናከርን አስፈላጊነት ገልጠዋል። የአፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት የማኅበራቸውን የ2009 ሽልማት ማሸነፉንም ይፋ አድርገዋል።

ኮንፈረንሱ ኅብረቱን ለሌላ ሦስት ዓመት የሚያገለግሉ ስምንት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን መርጧል። በዚህም መሠረት፣

1. ፕሬዚዳንት - የሴኔጋሉ የሕግ ባለሞያ አኪሬ ሙና በድጋሚ ተመርጠዋል።
2. ለማዕከላዊ አፍሪካ ም/ፕሬዚዳንትነት፣ ሚ/ር ጂን ሀጉማ፣ ከሩዋንዳ፣
3. ለምሥራቅ አፍሪካ ም/ፕሬዚዳንትነት፣ ሚ/ር ሀሺም አቡ በከር አልጃሊ፣ ከሱዳን፣
4. ለሰሜን አፍሪካ ም/ፕሬዚዳንትነት፣ ሚ/ር ጂሙር መሐመድ፣ ከቱኒዝያ፣
5. ለደቡብ አፍሪካ ም/ፕሬዚዳንትነት፣ ሚ/ር ኤሊጃህ ባንዳ፣
6. ለምዕራብ አፍሪካ ም/ፕሬዚዳንትነት፣ ሚ/ር ማሜ ገዳማ ጉዬ፣ ከሴኔጋል፣

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር አምባሳደር፣ ኪዳኔ በየነ ሕንፃ፣ 1ኛ ፎቅ በሚገኘው ጽ/ቤቱ ውስጥ ባደራጀው ቤተ መጻሕፍታችን (የመረጃ ማዕከል) ይጠቀሙ፡፡ አባላት ዌብሳይታችንን በመጠቀም የጥብቅና አገልግሎታቸውን ማስተዋወቅ ይችላሉ፡፡

የማኅበሩ ጽ/ቤት

## ወቅታዊ ጉዳይ

7. ለዋና ፀሐፊነት፣ ሚ/ር አኪንቶላ አንቶኒ አኪንቦቴ፣ ከናይጄሪያ
8. ለአቃቤ ንዋይነት፣ ሚ/ር ቶም አዲያምቦ አጂን፣ ከኬንያ ተመርጠዋል።

የኅብረቱ ኮንፈረንስ በተጨማሪም የኅብረቱን ተሰናባች ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት አዳምጦ አጽድቋል። የኅብረቱን መተዳደሪያ ደንብ፣ አንቀጽ 9/6 በማሻሻል የኅብረቱ ዋና ጽ/ቤት የሚገኝበት አገር የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ከአገሩ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት የተመረጠ ሌላ ሰው እስከሌለ ድረስ ያለምርጫ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቋሚ አባል እንዲሆን ወስኗል። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሆነዋል።

ጠቅላላ ኮንፈረንሱ ከዚህም በተጨማሪ፣

1. የሕግ ባለሙያዎችና የጠበቆች ማኅበራት በአፍሪካ ኅብረት አባል አገሮች የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ቴክኖሎጂያዊና በሌሎች ልማቶች ያላቸውን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በርካታ የአፍሪካ አገሮች ነፃ የሕግ ሙያ ማኅበራት የሚመሠረቱበትን ሕግ ያወጡ መሆናቸውን በማጤን፣ ቀሪዎቹ የአፍሪካ አገሮች ብሔራዊ የሕግ ሙያ ማኅበራት በልዩ ሕግ እንዲመሠረቱና ሙያውን በመምራትና በመቆጣጠር ተገቢ ሚና እንዲኖራቸው በማድረግ የበኩላቸውን ገንቢ እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪ አድርጓል።
2. የኒጀርን ሁኔታ በጥሞና ገምግሞ የምዕራብ አፍሪካ የኢኮኖሚ ማኅበ ረሰብና የአፍሪካ ኅብረት በኒጀር መንግሥትና በፕሬዚዳንቱ ላይ አገሪቱ የፈረመቻቸውን ውሎች፣ የአፍሪካ ኅብረት ማቋቋሚያ ሕጎችን፣ የአፍሪካ የሰብዓዊ መብትና የሕዝቦች ቻርተርን እንዲያከብሩ ጫና እንዲያደርጉ ጠይቋል።

1. የአፍሪካ ኅብረት አባል መንግሥታት ሁሉ ዐቢይ ስምምነቶችንና ፕሮጀክቶችን፣ በተለይ የአፍሪካን የሰብዓዊና የሕዝቦች መብት፣ የአፍሪካን የፍትህና የሰብዓዊ መብት ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ ፕሮቶኮልን፣ የአፍሪካ የምርጫ፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ቻርተርን እንዲያፀድቁ ጠይቋል።
2. የአፍሪካ ሰብዓዊ መብትን ለማስከበር ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ የተቋቋሙ የአፍሪካ ፍርድ ቤቶች ሥራ ቸው የተቀናጀ እንዲሆን የአፍሪካ የሰብዓዊና የሕዝቦች መብት ኮሚሽን የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግ ጥሪ አስተላልፏል።
3. የአፍሪካን ኢኮኖሚ ለማጠናከርና የአገሮችን ኢኮኖሚያዊ መብቶች ለማስከበር የሚያስችል የሕግ ምክር አገልግሎት እንዲጠናከር የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣
   - በጉዳዩ ላይ አንድ የታዋቂ የሕግ ባለሙያዎች ስብሰባ እንዲጠራ፣
   - በዚህ ስብሰባ የሚደረስበትን ስምምነት አትሞ እንዲያወጣ፣
   - መንግሥታትና የአፍሪካ ፓርላማ የሚደርስበትን ስምምነት ለማስፈፀም እንዲተባበሩ፣
   - የአፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ክርክሮች በብሔራዊም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲነሱ ከተደረሰበት ስምምነት አንፃር እንዲፈቱ እንዲያደርጉ ጠይቋል።

ኮንፈረንሱ በመጨረሻም፣

- የአፍሪካ መንግሥታት ዋና ዋና ዓለም አቀፍ ሰነዶችን፣ በተለይም ሕገ-መንግሥታዊነትን፣ ዴሞክራሲን፣ መልካም አስተዳደርንና ሰብዓዊ መብትን በተመለከተ የወጡ ስምምነቶችን ማፅደቃቸውን መከታተያ ሥርዓት እንዲኖር፣

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## በምሥራቅ አፍሪካ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ

ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ አካላት የሚደጋገፉብትንና የሚማማሩበትን መድረክ መፍጠርም ተጓዳኝ አላማው ነው።

ስብሰባው በካናዳ ጠበቆች ማህበር ለተጠቀሱት አካባቢዎች የተዘረጋውን ፕሮግራም ለማስተዋወቅና ለመረዳት፣ እንዲሁም በፍትህ ማዳረሱ ሥራ ረገድ የካናዳን ልምድ ለመቅሰም ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነ ከስብሰባው አዘጋጅና ከክልሉ ፕሮግራም ዳይሬክተር ከሚስ ጄኔፈር ከር መልዕክት መረዳት ይቻላል።

ከኢትዮጵያም በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማህበር አስተባባሪነት የጠቅላይ ፍርድ ቤቱን ምክትል ፕሬዚዳንት ጨምሮ ከፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከሕግና ፍትህ ማሻሻያ ተቋም፣ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር የተውጣጡ ስምንት ተሳታፊዎች ስብሰባው ላይ ተገኝተዋል። በስብሰባው መጨረሻም ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ሀገራዊ የሥራ ቡድን ለማደራጀት ስምምነት ላይ ተደርሷል። ☐

## የኢትዮጵያ የሕግ . . .

(ከገጽ 1 የዞረ

(Ethiopian Bar Association) ጠቅላላ ጉባዔውን በቅርቡ ይጠራል።

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔውን በየዓመቱ በታኅሣሥ ወር የሚያካሂድ ቢሆንም በበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማኅበራት አዋጅ መሠረት ራሱን አደራጅቶ ለመመዝገብ እንዲችል ጉባዔውን በጥቅምት ወር አጋማሽ ለማካሄድ ወስኗል።

በአሁኑ ጊዜ መተዳደሪያ ደንቡን ከአዋጁ አንፃር በመከለስና ራሱን እንደ አዲስ በማዋቀር ሂደት ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።☐

**ተሚጋች** – በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር በየሁለት ወር የሚታተም

ስልክ : 251-11-553-01-22
ፖ.ሣ.ቁ. : 700
ፋክስ : 251-11-515-2047
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ኢሜይል : eba@ethionet.et
ዌብሳይት : www.ethiopian-bar.org

## ወቅታዊ ጉዳይ

### የሕግ ባለሙያዎች . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ልማቶች ያላቸውን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃ የሕግ ሙያ ማኅበራት የሚመሠረቱበትን ሕግ ያወጡ መሆናቸውን አውስቷል፡፡

የአፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት (ፓሉ) በዘንድሮ ኮንፈረንሱ ካሳለፋቸው ውሳኔዎች አንዱ የኅብረቱን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9፣ ንዑስ አንቀጽ 6 በማሻሻል ዋና ጽ/ቤት የሚገኝበት አገር የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ከአገሩ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት የተመረጠ ሌላ ሰው እስከሌለ ድረስ ያለምርጫ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቋሚ አባል እንዲሆን ወስኗል፡፡ በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ስለሺ ቀፀላ የፓሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቋሚ አባል ሆነዋል፡፡

የፓሉ ኮንፈረንስ ካከናወናቸው ተግባራት አንዱ ኅብረቱን ለሌላ ሦስት ዓመት የሚያገለግሉ ስምንት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን መምረጥ ነበር፡፡ (የተመራጮችን ማንነትና ዝርዝር በገጽ 2 እና 3 ይመልከቱ)፡፡

የፓሉ ኮንፈረንስ ማጠቃለያ መግለጫ በመጨረሻም የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን፣ በተለይም ሰብሳቢው ክቡር ጂን ፒንግ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ኮንፈረንሱ እንዲሳካ ላደረጉት እገዛ አመስግኗል፡፡

የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት እንደተቋቋመ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ ምሥክር ወረቀት የተሰጠው ሲሆን ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የዋና ጽ/ቤት ስምምነት ለመፈራረም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥያቄ አቅርቦ ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ነው፡፡ □

### በባህር ላይ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የአለም የጠበቆች ማህበር 'Legalbrief AFRICA' በሚለው እትሙ እንደገፀው በአሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ አውሮፓ ኅብረትና ዴንማርክ መካከል በተደረገ ስምምነት ነበር በባህር ላይ ውንብድና የተጠረጠሩ ሶማላዊያን ወደ ኬንያ መጥተው እንዲዳኙ የተደረገው፤ ምንም እንኳን ውጤቱ አሉታዊ እንደምታ ቢኖረውም፡፡ በእትሙ መሠረት መቀመጫውን ፓሪስ፣ ፈረንሳይ ያደረገው የአለም ጠበቆች የሕግ እርዳታ ቅንጅት ስምምነቱ የተጠርጣሪዎችን ሰብዓዊ መብትና ጠበቃ የማግኘት መብትን የሚጥስ ነው ይላል፡፡

በሶማሊያ ድንበር አካባቢ በአውሮፓ ባህርተኞች አማካኝነት በቁጥጥር ስር ከዋሉት ተጠርጣሪዎች ውስጥ አርባ ለሚሆኑት የሕግ ድጋፍ የሚሰጠው የዚሁ የሕግ ቡድን ተወካይ የሆኑት አቢ ሲንግ እንደሚሉት ከመቶ የሚበልጡ በባህር ላይ ውንብድና የተጠረጠሩ ግለሰቦች ያለምንም የህግ እርዳታ ኬንያ ውስጥ ለፍርድ እንዲቀርቡ መደረጋቸው መሠረታዊ የሰብዓዊ መብታቸውን እና በአግባቡ የመዳኘት መብታቸውን እንደሚጥስ ለተባበሩት መንግስታት፣ ለአውሮፓ ኅብረት እንዲሁም ለኬንያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቀዋል፡፡

አያይዘውም ስለሁኔታው ሲገልፁ በኬንያ ሕግ መሠረት የሞት ቅጣት ሊያስከትሉ የሚችሉ የወንጀል ድርጊቶች ካልሆኑ በስተቀር በሌሎች የወንጀል ድርጊቶች የተከሰሰ ግለሰብ ነፃ የሕግ ድጋፍ ከመንግስት የሚያገኝበት አጋጣሚ የለም፡፡ ይህም ከላይ በተጠቀሰው ድርጊት የተጠረጠሩ ሶማሌያውያንን ከመንግሥት ሊያገኙት የሚገባውን የሕግ ድጋፍ እንዳያገኙ እንቅፋት ሆኗል ብለዋል፣ ተወካዩ፡፡ □

- የአፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት የዳርፉር ልዩ ኮሚቴና የአፍሪካ ኅብረት የዳርፉር ታዋቂ ሰዎች ኮሚቴ በአካባቢው የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን የሚያነጋግሩበት ሁኔታ እንዲመቻች፣
- ዓመታዊ የአገሮች የሕጋዊነት አከባበር ሁኔታ አመልካች (index) እንዲዘጋጅ፣ በአፍሪካ መልካም አስተዳደርን ለማጠናከር ከሞ ኢብራሂም መገምገሚያ ሥርዓት ጋር አብሮ ለመሥራት ወስኗል፡፡

## ም ሥ ጋ ና

የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት ኮንፈረንስ፣

- አፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን፣ በተለይም ሰብሳቢው ክቡር ጂን ፒንግ ለፓሉ ላላቸው አጋርነትና ለሰጡት ድጋፍ ያመሰግናል፡፡
- የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንትና የማኅበሩ ጽ/ቤት ኮንፈረንሱ እንዲሳካ ላደረጉት ድጋፍና መስተንግዶ አድናቆቱን ይገልፃል፣
- የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ በተለይም ፕሬዚዳንቱ ዶ/ር ዶናልድ ካቤሩካ ለመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት ላሳዩት አጋርነትና ለሰጡት ድጋፍ ከልብ ያመሰግናል፡፡
- የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት በተለይ ዶ/ር ሞ ኢብራሂም ንግግር እንዲያደርጉ የቀረበላቸውን የአጭር ጊዜ ጥያቄ በመቀበላቸውና የአፍሪካን ሲቪል ማኅበረሰብ በመደገፍ ለሚያደርጉት ጥረት ልዩ ምሥጋና ያቀርባል፡፡
- የአሜሪካ ብሔራዊ ጠበቆች ማኅበርና ፕሬዚዳንቱ ሚስተር ሮድኒ ግሪጐሪ ሙር በኮንፈረንሱ ላይ እንዲገኙ የቀረበላቸውን ግብዣ ተቀብለው በክብር እንግድነት በመሳተፋቸውና የማኅበራቸውን የ2009 ሮን ብራውን ሽልማት ለመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት በማበርከታቸው ልባዊ ምሥጋና ያቀርባል፡፡
- ለተሰናባቹ የመላው አፍሪካ የሕግ ባለሙያዎች ኅብረት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምሥጋና እያቀረበ ለአዲሱ አመራር መልካም ምኞቱንና ድጋፉን ይገልፃል፡፡

ተሰናባቹ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ኅብረቱን በማጠናከር፣ ከአፍሪካ ኅብረት፣ ከአፍሪካ ልማት ባንክና ከሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በማስተሳሰር ላስገኘው ውጤት ምሥጋና ያቀርባል፡፡ □

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ሐምሌ 12 ቀን 2001

# የሕግ አስከባሪ ተቋማት

*"አጠቃላይ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም" በሚል ርዕስ ተጠናቅሮ በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ለእትም ከበቃው ጥናት የተወሰዱ የተለያዩ የሕግ አስከባሪ ተቋማትን የሚመለከቱ ተከታታይ ፅሁፎችን ባለፉት እትሞቻችን ለንባብ ማብቃታችን ይታወሳል። ለዛሬም ማረሚያ ቤቶችንና የሕግ ትምህርትና ሥልጠናን አስመልክቶ ከተፃፈው ውስጥ ቀንጭበን እንደዚህ አቅርበነዋል።*

## ማረሚያ ቤቶች

የማረሚያ ሥርዓት ሕጋዊ ማዕቀፍ እ.ኢ.አ በ1944 የወጣው አዋጅ ቁጥር 45/1944 እንደሆነ ይነገራል። ይህ አዋጅ በአሁኑ ጊዜ ኃላ ቀርና ዋጋ የሌለው ነው። በአሁኑ ጊዜ አዲስ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ተዘጋጅቷል። የወንጀል ሕጉ የወንጀል ተጠያቂነትን፣ ቅጣትንና አመክሮን የተመለከቱ ድንጋጌዎች አሉት። የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓቱም ከፍርድ በፊት ተከሳሾች በእስር የሚቆዩበትን ሁኔታ የሚመለከቱ ጥቂት ድንጋጌዎች አሉት። በፖሊስ ጣቢያ የታሰሩ ሰዎችን የእስር ሁኔታ በሚመለከት ኃላፊነቱ የጣቢያው አዛዥ ነው። በፌዴራል ደረጃ ማረሚያ ቤቶችን በሚመለከት ኃላፊነቱ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ሲሆን በክልል ደረጃ ግን የፍትህ ቢሮዎች ነው። ማረሚያ ቤቶች ለተለያዩ አካላት ተጠሪ መሆን በመተባበርና በጋራ በመስራት ረገድ የራሱ የሆነ ውስብስብነት ይኖረዋል። የማረሚያ ቤት ፖሊሶች የመደበኛ ፖሊስ ሃይል አካል ካለመሆናቸውም በላይ ሥልጣናቸውም የተለየ ነው።

አቃቤ ሕግ በማረሚያ ቤቶች ያሉ እስረኞችን አያያዝ የመቆጣጠር ሥልጣን እንዳለው በንድፈሃሳብ ደረጃ የሚነገር ቢሆንም ተግባ ራዊነቱ ግን በጣም ውሱን ነው። የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ማረሚያ ቤቶችን ለመለወጥ ሃሳብ ያለው መሆኑ ይነገራል። በሚኒስቴሩ የተዘጋጀ አንድ ጽሁፍ ላይ እንደተገለፀው አዲስ ማረሚያ ቤት በአዲስ አበባ ለመገንባትና ዘርፈ ብዙ የሰው ሃይል አቅም ግንባታ ለማድረግ መነሳቱን ይገልፃል። በፅሁፍ ከተጠቀሱት የማሻሻያ ሃሳቦች መካከልም ኤሌክትሮኒክ የታራሚዎች ምዝገባ፣ የማረሚያ ቤት አስተዳዳሪዎች ማንዋል ማዘጋጀትንና የታራሚዎች የፍላጐት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ ይጠቀሳሉ። የኦሮሚያና የአማራ ክልል መንግሥታትም የራሳቸውን የማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ የማድረግ ሃሳቦች አሏቸው። በተለያዩ ማረሚያ ቤቶች፣ በፖሊስና በአቃቤ ሕግ መ/ቤቶች መካከል ያለው የመረጃ ፍሰት በግልፅ የሚታወቅ አይደለም። ለታራሚዎች የሚደረግ የሕግ እርዳታን በተመለከተም በጥቂት ጠበቆች ከሚሰጥ የተከላካይ ጠበቃነት አገልግሎት ውጭ ብዙም የተደራጀ ሥራ የለም።

አዲስ የተረቀቀው የማረሚያ ቤቶች ሕግ የእስረኞችን አያያዝና የእስር ሁኔታ በሚመለከት የያዛቸው ድንጋጌዎች በግርድፍ የሚታዩ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የወጣት ጥፋተኞችን አያያዝ በሚመለከት በወንጀል ሕጉ የተዛፉ ድንጋጌዎች ወደ ጎን ተትተዋል። በቀጠሮ ላይ ያሉና ፍርደኛ እስረኞች ተለያይተው እንዲታሰሩ የሚደነግገው ሕግም እንዲሁ።

ተጠርጣሪዎች በፖሊስ ተይዘው ምርመራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ በፖሊስ እስር ቤት ይቆያሉ። ይህም ረጅም ጊዜን ይፈጃል። ከዘጠኙ ክልሎች መካከል ስምንቱ ማረሚያ ቤቶች የተመለከተ ሕግ እስካሁን አላወጡም። ይህም በእስረኞች አያያዝ እና ተሐድሶ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ታፅዕኖ የሚያደርግ ነው። ምናልባትም የማረሚያ ቤቶች አንዱና ዋናው ችግርና ድክመት ተገቢ የሆነ የሥልጠና ሥርዓት አለመኖር ነው። ከዚህም በተጨማሪ የማረሚያ ቤት ሠራተኞችንና እስረኞችን ግንኙነት የሚመለከት ግልጽ ሕግ አለመኖርና የማረሚያ ቤቶችና የፖሊስ ማረፊያ ቤቶች ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው መሆን በተጨማሪ የሚታዩ ችግሮች ናቸው። በማረሚያ ቤቶች ባለው ደካማ አስተዳደር ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት የተቋቋሙት የእስረኞች ኮሚቴዎች በመሠረቱ በሕግ የታወቁ አካላት አይደሉም። በአገር አቀፍ ደረጃ ማረሚያ ቤቶችን የሚቆጣጠር ገለልተኛ አካል የለም። ለማረሚያ ቤቶች የሚመደበው በጀትም ማረሚያ ቤቶችን ለማሻሻል ቀርቶ የእለት ተእለት ሥራዎችን ለማከና ወንም በቂ አይደለም።

## የሕግ ትምህርትና ሥልጠና

የሕግ ከፍተኛ ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረው እ.ኢ.አ በ1960ዎቹ አጋማሽ ከአዲስ አባባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ መከፈት ጋር ተያይዞ ነው። እ.ኢ.አ በ1974 በተከሰተው አብዮት ምክንያት በርካታ የውጭ መምህራን ከአገር ሲወጡ የማስተማሩ ሥራ በአብዛኛው የመጀመሪያ ዲግሪ ባላቸው መምህራን የሚካሄድ ሆነ። የወታደራዊው አገዛዝ እ.ኢ.አ በ1991 ከተወገደ በኋላ የግል የሕግ ትምህርት ተቋማትም ብቅ ማለት ጀምረዋል። ክልላዊ ዩኒቨርስቲዎችም በብዙ ክልሎች ተቋቁመዋል።

በአሁኑ ጊዜ የሕግ ትምህርት የሚሰጡ ስድስት የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎችና ዕውቅና ያላቸው አምስት የግል ኮሌጆች ይገኛሉ። በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው የከፍተኛ ትምህርት ማስፋፊያ ፕሮግራም የሕግ ትምሕርት መስፋፋትን የሚያጠቃልል ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ የሕግ ምሩቃንን የሚመዘግብ ብሄራዊ የምዝገባ ስርዓት ያለ አይመስልም። በአሁኑ ጊዜ ለአገሪቱ የሚያስፈልገው ሙሩቃን ቁጥር በሚገባ መጠናትና ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው።

ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በመመካከር በጀት የሚመድበው የፌዴራሉ ትምህርት ሚኒስቴር ነው። የሕግ ትምህርት ክፍሉ የሌላ ፋኩሊቲ አባል ሆኖ በተደራጀባቸው ዩኒቨርስቲዎች ከሌሎች ተቋማት ጋር የመወዳደር አቅማቸው የደከመ ነው። በአገሪቱ የሰለጠኑ ዳኞች፣አቃብያነ ሕግ ፣ጠበቆች ሌሎች የሕግ ሞያተኞች እጥረት እንዳለ ይታወቃል። ምንም እንኳን በሥራ ላይ ያሉትን ሞያቸውን የማሻሻል ሥልጠና አስፈላጊነቱ የታመነበት ቢሆንም በዚህ ረገድ በቂ ሥራ ተሰርቷል ማለት አይቻልም።

የሕግ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱን በሚመለከት በመንግሥት ሊታሰብበትና የግድ ሊሆን የሚገባው አንድ ጉዳይ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በፍትህ ሚኒስቴርና በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር መካከል ያለው ድርሻ ምን እንደሆነ ነው። በዩኒቨርስቲዎች አዲስ የተከፈቱት የሕግ ተ/ቤቶች ስኬታማ መሆን በአብዛኛው በአገር ውስጥና በውጭ ካሉ መሰል የሕግ ትምህርት ተቋማት ጋር በሚያደርጉት ትብብርና መደጋገፍ ላይ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ የሕግ ሥርዓት ትምህርት ዝግጅትና ወቅታዊ የማስተካከል ሥራዎች በበቂ ሁኔታ አይሰሩም። የጥናትና ምርምር ሥራም ገና አልዳበረም። ☐

ይህ እትም ለንባብ የበቃው ከኢኒሼቲቭ አፍሪካ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።